# መቅድም

በማኅበረ ቅዱሳን የጥናትና ምርምር ማእከል ሥር የሚዘጋጀው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥናት መጽሔት ቅጽ ፱ በጸሓፊዎች እና አርታዒዎች ያላሰለሰ ጥረት እነሆ ለኅትመት በቅቷል። ሁላችንንም እንኳን ደስ አለን።

ይህ ቅጽ እንደቀደምቶቹ ቅጾች በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የቀረቡ በአጠቃላይ ስድስት ጽሑፎችን የያዘ ነው። ሦስቱ በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ ሲሆኑ፣ ሦስቱ ደግሞ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የቀረቡ ናቸው። ጽሑፎቹ በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሕይወት፣ በተማሪዎች መንፈሳዊ ትምህርት ተመክሮ እና በቤተ ክርስቲያን ውስጥና በሃይማኖቶች መካከል ያሉ ግጭቶችን በመተንተን ላይ ያተኮሩ ናቸው።

የመጀመሪያው ጽሑፍ በ፲፰ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተወልደው፣ በ፲፱ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ተጽዕኖ ፈጣሪ የነበሩትን የአለቃ ምላት ምሕረትን የሕይወት ታሪክ የሚያትት ሲሆን፣ በጽሑፉ ስለትውልዳቸው፣ ስለአስተዳደጋቸው፣ ስለተማሩባቸው እና ስለአገለገሉባቸው አድባራት፣ በሕይወታቸው ስለገጠማቸው ፈተና ያትታል። ጽሑፉ የአለቃ ምላትን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና መንፈሳዊ ሕይወት የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን፣ ሰውየው በቤተ መንግሥቱም በኩል የንጉሥ አማካሪ እስከመሆን የደረሱበትን ጉዞ በአብነት በማንሳት የቀደሙ አባቶች የነበራቸውን ዘርፈ ብዙ ሚናና አገልግሎት በእሳቸው ሕይወት አማካኝነት አቅርቧል።

ሁለተኛው ጽሑፍ ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ተሳታፊ ስለሆኑ የቆሎ ተማሪዎች የሚያትት ነው። ጽሑፉ በግል ተሞክሮ፣ በመስክ ምልከታ እና በቃለ መጠይቅ የተገኘን መረጃ ዋቢ በማድረግ በተለምዶ የቆሎ ተማሪዎች ስለሚባሉ የአብነት ተማሪዎች ልዩ የትምህርት ጉዞ የሥነ ባህል ጥናትን መሠረት በማድረግ በሰፊው ትንተና ሰጥቷል። ከተነሡት ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል ተማሪዎቹ ምግባቸውን ለምን እና እንዴት ለምነው እንደሚበሉ፣ የትምህርት አሰጣጡ ምን እንደሚመስል እንዲሁም በተማሪዎች መካከል ያለው መንፈሳዊና ማኅበረሰባዊ መስተጋብር ለመማር-ማስተማር ሂደቱ ምን አስተዋጽኦ እንዳለው በጥልቀት የተተነተነበት በአብነት ይጠቀሳሉ።

ሦስተኛው ጽሑፍ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሀብት የሆኑት ጾም፣ ጸሎት፣ ይቅርታ እና ማኅበረሰቡ ተሳትፎ የሚያደርግባቸው በጎ ተግባራት ለመንፈሳዊ እና አካላዊ ደኅንነት ጠቀሜታ እንዳላቸው ይገልጻል። በጤና በተለይም

ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን በመከላከል ረገድ ያላቸውን ሚና እና ልዩ ተፅዕኖ በዝርዝር አቅርቧል። ጽሑፉ እነዚህ የሕይወት መርሖዎች ከሥነ ምግብ፣ ከአካላዊ እንቅስቃሴ፣ ከሥነ አእምሮ እና ሥነ ማኅበራዊ የጥናት መስኮች አንጻር ምን ዓይነት አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ በመተንተን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለማኅበራዊ እና ለግላዊ ሕይወት መስተካከል ላይ ያላትን አስተዋፅኦ ለአንባብያን አድርሷል።

አራተኛው እና አምስተኛው ጽሑፎች በግጭት ላይ ያተኮሩ ናቸው። አራተኛው ጥናት የሃይማኖት ብሔርተኝነት በሚፈጥረው የግጭት ምንነት፣ ሰበብ እና ተዋናይ አካላትን በመለየትና በመመርመር ላይ ያተኮረ ነው። ይህ ጥናት ገላጭ የጥናት ዘዴን የተጠቀመ ሲሆን፣ የወሊሶ አካባቢ ግጭቶችን መነሻ በማድረግ የደረሰበትን ግኝት አቅርቦ ወደፊት ቤተ ክርስቲያን ምን ማድረግ እንዳለባት ምክረ ሐሳቡን አስቀምጧል። አምስተኛው ጽሑፍ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በልዩ ልዩ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መካከል እንዲሁም በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እና በቤተ ክርስቲያን የአህጉረ ስብከትም ሆነ ማእከላዊ አስተዳደር መካከል ያሉ ግጭቶችን ምንነት፣ ዓይነት እና ምክንያት በዝርዝር አቅርቦ እነዚህን ግጭቶች ለመፍታት የተሄደባቸውን ሂደቶች ከውጤታቸው ጋር አቅርቧል። ጥናቱ ቤተ ክርስቲያንን መነሻ ያደረጉ ግጭቶች እንዳይከሠቱ፣ ከተከሠቱም እንዴት ሊፈቱ እንደሚችሉ የራሱን ምክረ ሐሳብ ሰንዝሯል።

ስድስተኛው ጽሑፍ በየአቡ ሰይፌን የሴቶች አንድነት ገዳም ተዘጋጅቶ በአዜብ በርሄ የተተረጎመውን *ዝክረ ቅዱሳት አንስት ዘተዋሕዶ -፩* የተባለውን መጽሐፍ የሚዳስስ ነው። ጽሑፉ መጽሐፉን ምዕራፍ በምዕራፍ ከዳሰሰ በኋላ፣ የመጽሐፉን ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች አሳይቷል። ጽሑፉ የቅዱሳት አንስት ታሪክ አሁን ላለው ትውልድ መማሪያ እንደሚሆን በማሳየት የመጽሐፉን ጠቃሚነት አትቷል።

ይህ ቅጽ ለኅትመት እንዲበቃ ጽሑፋቸውን በማበርከት እና ተከታታይ የማስተካከያ እና የማብራሪያ ጥያቄዎችን በመመለስ ሳይሰለቹ እስከመጨረሻው ጽሑፋቸው ይህንን ቅርጽ ይዞ እንዲወጣ ላደረጉ ጸሓፊዎች ምስጋናችን ይድረሳችሁ። ጽሑፎቹን በመገምገም እና ገንቢ አስተያየቶችን በመስጠት የተሳተፋቹሁ ባለሙያዎች ያለናንተ አስተዋፅኦ መጽሔቱ ሊታተም አይችልም ነበርና እጅግ በጣም እናመሰግናለን። አንባብያንን ደግሞ በቀጣይ ለምናሳትመው ቅጽ ፲ ጽሑፉችሁን እንድታቀርቡልን እንጋብዛለን።

**አመሰግናለሁ!**

**ደርብ አዶ (ፒ.ኤች.ዲ.)**

**የመጽሔቱ ዋና አርታዒ**

# Preface

The 9th volume of the Journal of Ethiopian Church Studies published by the Research Center of Mahibere Kiduan has been published through the tireless efforts of the writers and editors. Congratulations to all of us!

This volume, like the previous ones, contains a total of six articles, three of which are written in Amharic and three of which are in English. The articles present analyses of the life of church scholars, the life of students in the church, and inter- and intra-religious conflicts in the context of EOTC.

The first article presents the life history of Alaka Milat Mheriet, who was born in the 18th century and was influential in church education in the 19th century. The article shows not only the life of Alaka Milat in the church, but also his journey to become the king's advisor in the palace. Hence, the article presents the life of the church fathers in light of his life.

The second article is about students studying in the educational system of the Ethiopian Orthodox Tewahdo Church. The article provides a comprehensive analysis based on folkloric/cultural research on the unique life experiences of the students, who are commonly called yäk'olo tämari, based on field observations and interview data. Among the main issues raised are why the students beg for their food, and how the students' lives can be considered as an independent cultural folk group or community.

The third article presents, in detail, the role and special impact of principles that promote spiritual and physical well-being, such as fasting, prayer, forgiveness and community participation, which are the assets of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church, in health - especially in preventing non-communicable diseases. The article analyzes the contribution of these principles from the perspective of nutrition, physical activity, psychology and sociological fields of

study and brings to the readers the contribution of the Church to the betterment of social and personal life.

The fourth and fifth articles focus on conflicts. The fourth study is focused on identifying and analyzing the nature, causes and actors of conflict due to religious nationalism. This research, using a descriptive research method and based on the conflicts in the Wäliso area, presents its analysis and puts forward the recommendations of what the church should do in the future. The fifth article also provides details of the types and causes for conflicts within the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church between different parish churches and between parish churches and the administration of the church's diocese and center. The article outlines the different mechanisms that EOTC uses to resolve suh conflicts and recommends further actions to prevent future conflicts.

The sixth article deals with the book "Zïkrä Qïdïsat Anïst Zätäwahïdo-1" compiled by Abu Sayfin Women's Unity Monastery and translated by *Azeb Bärhe*. The article explores the book chapter by chapter and presents the strengths and weaknesses of the book. The review prents the importance of the book as the history of the female saints would serve as a lesson for the present and future generations.

We would like to express our gratitude to the authors, who contributed their articles and tirelessly answered a series of questions for correction and clarification, and made the publication of this volume with the current state of the articles a reality. We also extend our gratitude to the experts who reviewed the articles and gave constructive comments. The journal would not have been published without your contribution. Finally,we invite readers to submit your manuscripts for publication in the upcoming issues.

**Thank you!**

**Derib Ado, PhD**

**Editor-in-chief of JECS**